


# የዩኤስ የአዋቂዎች ፓስፖርቶች

## 16 ዓመትና ከዚያ ዕድሜ በላይ ለሆኑ

### የፓስፖርት ደብተርና የፓስፖርት ካርድ

- የፓስፖርት ደብተር የሚያገለግለው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በአየር፣ በየብስና በባህር ሲገቡ ይሆናል።
- የፓስፖርት ካርድ የሚያገለግለው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በየብስና በባህር ሲገቡ ብቻ ነው፤ ሆኖም ግን ለዓለም አቀፍ የአየር ጉዞ አያገለግልም።
- የፓስፖርት ካርድ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ በየብስ ኬላ ጣቢያዎች ባሉ ዝግጁ በሆኑ የመግቢያ መስመሮች ሲገቡ ሊገለገሉበት ይችላሉ።
- 16 ዓመት ወይም ከዛ በላይ እድሜ ለሆኑ የሚሰጠው ፓስፖርት ለ10 ዓመታት ያገለግላል።
- የፓስፖርት ካርድ መጠኑ የክሬዲት ካርድን ያክላል ስለሆነም እንደመታወቂያም ሆኖ ሊያገለግል ይችላል።
- ደብተሩንና ካርዱን በአንድ ግዜ ለማግኘት ማመልከት ወጪን ይቀንሳል።




## ለፓስፖርት ለማመልከት የሚያስፈልግዎ:-

- ዩናይትድ ስቴትስ ዜጋ መሆንዎን ማረጋገጫ፤ ለምሳሌ እንደ ዩናይትድ ስቴትስ የልደት ምስክር ወረቀት።
- ፎቶ ያለበት በመንግስት የተሰጠ መታወቂያ።
- አመልካች ፓስፖርቱን በደብዳቤ ለማደስ ብቁ ካልሆኑ በአካል ቀርበው ማመልከት ይኖርባቸዋል።
- አንድ መጠኑ 2”x2” የሆነ የቀለም ፎቶ።
- የፓስፖርት ማመልከቻ DS-11.
- የፓስፖርት ክፍያ።

## ለተጨማሪ መረጃ

1-877-487-2778 (እንግሊዘኛና ስፓኒሽ)
ወይም 1-877-874-7793 TDD/TTY
travel.state.gov/passports